የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የሲዳማ ህዝበ ውሳኔ አፈጻጸም ሪፖርት

**ጥር 2012 ዓ.ም.**

**አዲስ አበባ**

# ማውጫ

**መግቢያ** ...... **III**

**ምዕራፍ አንድ** ...... **5**

**1. የቅድመ ዝግጅት ስራዎች** ...... **5**

1.1 ለህዝበ ውሳኔው ማስፈጸሚያ ዝርዝር ዕቅድና በጀት ዝግጅት ሂደት ...... 5

1.2 የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት...... 7

1.3 የምርጫ ሂደት የቅፃ ቅፆችና ቁሳቁሶች ዝግጅት...... 9

1.4 ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይቶችን ማድረግ...... 11

*1.4.1 ወደ ሀዋሳ የቴክኒክ ቡድን መላክ...... 12*

*1.4.2 ከደ/ብ/ብ/ሕ ክልል፣ ከሲዳማ ዞን እና ከጸጥታ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች...... 12*

1.5 የህዝበ ውሳኔ ማስፈፀሚያ ማንዋል ማዘጋጀት...... 12

1.6 የሲዳማ ህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎችን መቅጠር፣ መመልመል እና ማደራጀት ...... 13

*1.6.1 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች የመምረጫ መስፈርቶች ...... 13*

*1.6.2 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ምዝገባ እና አመራረጥ...... 13*

*1.6.3 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች መረጃ ማደራጀት እና ምደባ...... 14*

1.7 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ስልጠና ...... 15

*1.7.1 የአሰልጣኞች ስልጠና...... 16*

*1.7.2 የህዝበ ውሳኔ የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች ስልጠና...... 16*

1.8 የአስፈፃሚዎች ምደባና ስምሪት...... 17

**2. የምርጫ ወቅት ክንውን** ...... **18**

2.1 የህዝበ ውሳኔ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ድልድል እና ስርጭት ...... 18

2.2 የድምጽ መስጫ ወረቀት እና ፖስተር ዝግጅት ...... 19

2.3 የመራጮች ምዝገባ ...... 19

2.4 የመራጮች ትምህርት እና መረጃ ተደራሽነት ...... 20

*2.4.1 የህዝበ ውሳኔውን የጊዜ ሰሌዳዎች አስመልክቶ ለማህበረሰቡ መረጃ መስጠት...... 21*

*2.4.2 የመራጮች መረጃና ጥቆማ መስጫ የስልክ መስመር ( hot line)...... 21*

2.5 የምርጫ ጸጥታ እና ደህንነት...... 22

2.6 የድምፅ መስጠት ሂደት...... 22

*2.6.1 ለተጨመሩ ምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚዎች ስምሪት...... 23*

*2.6.2 የድምፅ አሰጣጥና ቆጠራ...... 23*

**3. ድህረ ምርጫ** ...... **24**

3.1 ውጤት አገላለጽ...... 24

3.2 በቦርዱ የጸደቀ የምርጫ ውጤት...... 24

3.3 በምርጫ ክትትል የተሰሩ ሥራዎች...... 25

3.4 የሲዳማ ህዝበ ውሳኔ የበጀት አጠቃቀም ...... 26

**4. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ከህዝበ ውሳኔው የተገኙ ትምህርቶች** ...... **28**

4.1 በህዝበ ውሳኔው የሲቪል ማህበራትና የሚዲያ ተሳትፎ ...... 28

4.1.1 ሲቪል ማህበራት እና የህዝበ ውሳኔው መታዘብ ሂደት -...... 28

4.1.2 የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የመታዘብ ሂደት ...... 29

4.2 ከህዝበ ውሳኔው የተገኙ ዋና ዋና ትምህርቶች ........ 30
4.2.1 የህዝበ ውሳኔው አጠቃላይ አፈጻጸም ላይ የተገኙ ዋና ዋና ትምህርቶች ........ 30
4.2.2 የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላ........ 32
4.2.3 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ስልጠናን በተመለከተ ........ 32
4.2.4 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ስምሪት ........ 33
4.2.5 የምዝገባ እና ድምጽ መስጠት ሂደት ሰነድ ህትመት፣ ድልድል፣ ርክክብ እና ስርጭት ........ 33
4.2.6 በመራጮች ምዝገባ ሂደት ወቅት ........ 34
4.2.7 በድምፅ መስጫ ቀን ........ 34
4.2.8 በምርጫ አስፈፃሚዎች አስተዳደር ........ 35
4.2.9 የድምፅ ቆጠራ ውጤት አሞላል፣ አላላክ እና ይፋ አደራረግ ........ 35

**ማጠቃለያ ........ 37**

**ምስጋና ........ 38**

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በህገ መንግስቱ፣ በማቋቋሚያ እና በምርጫ እና የፓለቲካ ፓርቲዎች አዋጆች 1133/2011 እና 1162/2011 በተሰጠው ስልጣን መሰረት አጠቃላይ ፣የአካባቢ፣ የድጋሚ፣የማሟያ ምርጫዎችን እና ህዝበ ውሳኔዎችን የማካሔድ ሃላፊነት ያለበት ተቋም ነው። በዚህም መሰረት በአገሪቷ ውስጥ የሚደረጉ ማንኛውንም አይነት ምርጫዎችን ሲያስፈጽም ቆይቷል።

በዚሁ መሰረት የደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በቁጥር ክም/አ/9/7092/2011 በቀን 12/3/2011 በተፃፈ ደብዳቤ የሲዳማ በክልልነት የመደራጀት ጥያቄን አስመልክቶ ቦርዱ ህዝበ ውሳኔ እንዲያደራጅለት ጥያቄ አቅርቧል።

ቦርዱም ይህንን ጥያቄ ተከትሎ የህዝበ ውሳኔውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ የተለያዩ ዝግጅቶችን በማድረግ የአፈፃፀም የድርጊት መርሀ ግብር እና በጀት በማዘጋጀት፣የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ህዝበ ውሳኔውን ህዳር 10 ቀን 2012 ዓ.ም ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ አከናውኗል።

በመሆኑም አጠቃላይ የህዝበ ውሳኔ አፈፃፀም ከቅድመ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ድህረ ምርጫ ድረስ የተከናወኑ ተግባራት፣ያጋጠሙ ችግሮች እና ለወደፊት የመፍትሄ ሃሳብ ዝርዝር በዚህ ሪፖርት ውስጥ ተካቷል።

በዚህ ሪፖርት ዝግጅት ወቅት የየወረዳዎቹ አስተባባሪዎች ያዘጋጁትን ሪፖርት በግብአትነት በመጠቀም፣ በክትትል፣ በመስክ ጉብኝት እና መረጃ በማሰባሰብ የተገኙ ሰነዶችን በማደራጀት፣እና በቅሬታ መልክ የቀረቡ ዝርዝር መረጃዎችንና ዶክመንቶችን በአባሪነት ማካተት ተችሏል።

የመጀመሪያው ምዕራፍ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ማለትም የእቅድ ዝግጅት፣የምርጫ ማስፈፀሚያ በጀት ማዘጋጀት፣የምርጫ ጣቢያ ማደራጀትና  የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላና ስልጠና እንዲሁም የህዝብ ውሳኔ ማስፈፀሚያ ሰነዶች ዝግጅት፣ ህትመት ፣ድልድል እና ስርጭት እንዲሁም የቁሳቁስ ግዢን የሚያካትት ነው።

ሁለተኛው ምዕራፍ በምርጫ ወቅት የተከናወኑ ተግባራትን፣ የመራጮች ምዝገባን፣ የመራጮች ትምህርት፣ ድምጽ መስጠትን እና ሌሎች ተጓዳኝ ስራዎች የተከናወኑባቸውን ጉዳዮች በዝርዝር የሚተነትን ነው፣ በዚህ ሂደት ህዝበ ውሳኔ በሰላም እንዲጠናቀቅ የተሰሩ ስራዎችንም ያጠቃልላል።

ሶስተኛው ምዕራፍ የድምጽ ቆጠራ እና ውጤት አገላለጽ ጋር ተያይዞ ያሉ ጉዳዮች የሚዳሰሱበት ምዕራፍ ነው። የህዝበ ውሳኔው የበጀት አጠቃቀም በዚህም ምእራፍ ተካቷል።

አራተኛው ምዕራፍ በሲዳማ ህዝበ ውሳኔ አፈፃፀም ሂደት የታዛቢ ሲቪል ማህበራት ተሳትፎ እና ከሚዲያ ጋር የተገናኙ ስራዎች ተካተውበታል። የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶችና የተገኙ ልምዶችን ይዳስሳል።

# ምዕራፍ አንድ

# 1. የቅድመ ዝግጅት ስራዎች

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ህዳር 10 ቀን 2012 ዓ.ም ለተካሄደው የሲዳማ ህዝበ ውሳኔ የሚረዱ የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን አከናውኗል።

ቦርዱ በዝግጅቱ ህዝበ ውሳኔው ሰላማዊ እና ተአማኒ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ያደረገ ሲሆን በቅድመ ዝግጅት ከተሰሩ ስራዎች መካከል የህዝበ ውሳኔ ማስፈጸሚያ ዕቅድ ዝግጅት፣በጀት እና የድርጊት መርሀ ግብር ማዘጋጀት፣ የቅጻቅጽ እና የጊዜ ሰሌዳ ዝግጅት፣ መረጃ ማደራጀት፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በአፈጻጸም ዝርዝር ጉዳዮች እንዲሁም በምርጫ ጸጥታ እና ደህንነት ዙሪያ ውይይት ማድረግ፣ የምርጫ አስፈጻሚዎችን መመልመል እና ስልጠና መስጠት ከዋና ዋናዎቹ ወስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

## *1.1 ለህዝበ ውሳኔው ማስፈጸሚያ ዝርዝር ዕቅድና በጀት ዝግጅት ሂደት*

የሲዳማ ህዝበ ውሳኔን በተቀመጠለት ገደብ ለማጠናቀቅ ለማስፈጸሚያ የሚውል ዝርዝር እቅድና በጀት ማዘጋጀት ከቅድመ ዝግጅት ስራዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ተግባር ነበር። በዚሁ መሰረት ዝርዝር በጀት ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ዋና ዋና መነሻ ነጥቦች እና የተሰሩ ተግባራት በዝርዝር ቀርበዋል።

ለበጀት አሠራር መነሻ እንዲሆኑ በ2007 የጠቅላላ ምርጫ ላይ ስራ ላይ የዋሉ 24 ወረዳዎችን መነሻ በማደረግ በስራቸው 15 ማስተባበሪያ ማዕከላት ያደራጀ ሲሆን 1692 ምርጫ ጣቢያዎችን በ15ቱ ማስተባበሪያ ማዕከላት ስር አደራጅቶ ምርጫውን ለማስፈጸም በጀት በማቀድ ተንቀሳቅሷል።

ቦርዱ ለሲዳማ ህዝበ ውሳኔ የድምፅ ሰጪዎችን ቁጥር ለመገመት ይረዳዉ ዘንድ በማዕከላዊ ስታስቲክስ እድሜው ለድምፅ ሰጪነት የደረሰ ተብሎ የተገመተዉን አሀዝ መነሻ አድርጎ 5% በመጨመር 2,087,000 (ሁለት ሚሊዮን ሰማኒያ ሰባት ሺህ) የሚጠጋ ሕዝብ በድምፅ ሰጪነት ይመዘገባል በሚል ግምት መነሻ ዝግጅቶችን አከናውኗል።

| ተ.ቁ | የወረዳ ማስተባበሪያ | የመራጭ ህዝብ ግምት (ዕድሚያቸው 18 እናበላይ) | የ2019 ግምት ላይ 5% ተጨምሮ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሸበዲኖ፣ለኩ፣አቤላ | 141,145 | 148,202 |
| | ሃዋሳ ከተማ | 282,103 | 296,208 |
| 2 | ሀዋሳ ዙሪያ | 70,979 | 74,527 |
| 3 | አርቤጎና እና ሻፋሞ | 72,969 | 76,617 |
| 4 | ዳሌ፣ይርጋለም፣ | 152,455 | 160,078 |
| 5 | አለታወንዶ እና አለታወንዶ ከተማ | 117,673 | 123,557 |
| 6 | ዳራ እና ዳራ ኢትልቻ | 94,620 | 99,351 |
| 7 | ሁላ | 62,304 | 65,419 |
| 8 | በንሳ | 133,626 | 140,307 |
| 9 | አሮሬሳ ና ሆኮ | 88,193 | 92,603 |
| 10 | ቦርቻ | 145,898 | 153,193 |
| 11 | ጎርቼ | 60,085 | 63,089 |
| 12 | ማልጋ | 62,503 | 65,628 |
| 13 | ወንሸ | 53,331 | 55,998 |
| 14 | ሎካ አባያ | 58,663 | 61,596 |
| 15 | ጭሬ | 62,503 | 65,628 |
| 16 | ቡርሳ | 57,246 | 60,108 |
| 17 | አለታ ጩኮ | 103,641 | 108,823 |
| 18 | ቦና ዙሪያ | 63,968 | 67,166 |
| 19 | ወንዶገነት | 93,058 | 97,711 |
| | ድምር | **1,976,963** | **2,075,809** |

***ሰንጠረዥ 1: የተገመተ መራጭ ህዝብ ብዛት በወረዳ ስርጭት***

***ምንጭ፡ ማእከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን***

ለበጀት አወሳሰን ይሆን ዘንድ የህዝበ ውሳኔውን የሚያስፈጽሙ አስፈፃሚዎችን በ15 ማስተባበሪያ ቢሮዎች ለእያንዳንዳቸዉ ሁለት ወይም ሶስት ምርጫ አስፈጻሚዎች በድምሩ **32** (ሰላሳ ሁለት) የወረዳ አስተባባሪዎች እንዲሁም ለእያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ደግሞ 3 (ሶስት) የህዝበ ውሳኔ ምርጫ አስፈጻሚዎች በድምሩ 5076 እና 826 ተጠባባቂዎችን ጨምሮ **5902 (አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሁለት)** አስፈፃሚዎች በጠቅላላ የወረዳ አስተባባሪዎችን ጨምሮ 5934 (አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አራት) አስፈጻሚዎች በህዝበ ውሳኔው ላይ ይሳተፋሉ በሚል እቅድ ዝግጅቶች ተከናውነዋል፡፡

ለህዝበ ውሳኔ ማስፈጸሚያ የሚውል ዝርዝር በጀት ማለትም ለአገልግሎት እና ቁሳቁስ ግዢ፣ ለህትመት፣ የውሎ አበል፣ነዳጅ፣ እና ስራ ማስኬጃ እንዲሁም ለህዝበ ውሳኔ ምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠና የሚያስፈልግ ወጪ እና ሌሎች ተያያዥ ወጪዎች በማካተት ተዘጋጅቷል፡፡ በጀቱም ለደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ምክር ቤት ተልኮ የጸደቀ ሲሆን በአጠቃላይ **75,615,015(ሰባ አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አስራ አምስት ሺ ከአስራ አምስት)** ብር ህዝበ ውሳኔውን ለማስፈጸም በቦርዱ አካውንት ገቢ ተደርጓል፡፡

በእቅድ ዝግጅት ወቅት ከተከናወኑ ስራዎች መካከል የግዢ እና አገልግሎት እቅድ ሲሆን የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎችን ወደ ወረዳ የሚያጓጉዙ አውቶብሶች አገልግሎት ግዢ፣ የድምፅ መስጫ ሳጥን፣የምርጫ ማረጋገጫ ቀለም፣ለህትመት የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎች እና ቁሳቁሶችን በብዛት መጠንና ዓይነት በመለየት ግዢ ተከናውኗል፡፡

## *1.2 የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት*

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሲዳማ በክልልነት የመደራጀት ጥያቄ ህዝበ ውሳኔ በእቅድ እና በተያዘለት ፕሮግራም እንዲጠናቀቅ የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ አውጥቷል፡፡ የጊዜ ሰሌዳውም ለህትመት፣ለሰነድ ዝግጅት፣ ለድልድል እና ስርጭት ወቅትን፣ እና የክልሉ መንግስት ለቦርዱ ጥያቄውን ያቀረበበት ጊዜ እና ከዚያ ጋር ተያይዞ የተነሱ የተለያዩ ጥያቄዎችን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት እንዲጸደቅ ተደርጓል፡፡ በቦርዱ የፀደቀው የጊዜ ሰሌዳ ለምርጫ አፈፃፀም ክትትል እንዲረዳ ለክልል እና ዞን አስተዳደር አካላት፣ ለዞን አስተባባሪዎች እና ለወረዳ ምርጫ አስተባባሪዎች እና ለድምፅ መስጫ ጣቢያ ምርጫ አስፈፃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

## *የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ*
## *በ2012 ዓ.ም የሲዳማ በክልልነት የመደራጀት ጥያቄ ለሚካሄደው ህዝበ ውሳኔ አፈፃፀም የተዘጋጀ የጊዜ ሰሌዳ*

| ተ.ቁ | ክንውን | ቀን |
|---|---|---|
| 1 | በህዝበ ውሳኔው የጊዜ ሰሌዳ እና የህዝብ ውሳኔ ማስፈጸሚያ ማብራሪያ ላይ ውይይት የሚደረግበት | መስከረም 6 ቀን 2012 ዓ.ም. |
| 2 | የህዝበ ውሳኔው ምልክት በመምረጥ ለቦርዱ የሚያሳውቁበት | መስከረም 7 ቀን 2012 ዓ.ም. |
| 3 | ቦርዱ የህዝብ ውሳኔ ምርጫ የምልክት እና የአማራጭ ስሞችን ለህዝብ በሚዲያ ማሳወቅ | መስከረም 13 ቀን 2012 ዓ.ም. |
| 4 | የህዝበ ውሳኔ ቅስቀሳ ጉዳይ ላይ መወያየት | ከመስከረም 14-15 ቀን 2012 ዓ.ም. |
| 5 | የምርጫ ጣቢያ ዝግጅት | ጥቅምት 25 ቀን 2012 ዓ.ም. |
| 6 | የህዝበ ውሳኔ ቅስቀሳ የሚካሄድበት ጊዜ | ከጥቅምት 25-30 ቀን 2012 ዓ.ም. |
| 9 | ለህዝበ ውሳኔው ድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ የሚከናወንበት | ከጥቅምት 27 - ህዳር 6 ቀን 2012 ዓ.ም. |
| 10 | የህዝበ ውሳኔው የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ክፍት ሆኖ የሚቆይበት | ህዳር 7 ቀን 2012 ዓ.ም. |
| 11 | ስለህዝበ ውሳኔው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ለህዝቡ ገለፃ የሚሰጥበት | ህዳር 7 ቀን 2012 ዓ.ም. |
| 12 | የህዝበ ውሳኔው ቅሬታ በየደረጃው የሚቀርብበት እና ውሳኔ የሚሰጥበት | ከጥቅምት 26 - ህዳር 15 ቀን 2012 ዓ.ም. |
| 13 | የህዝበ ውሳኔው የድምፅ መስጫ ዕለት | ሕዳር 10 ቀን 2012 ዓ.ም. ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓት |
| 14 | የህዝበ ውሳኔው የድምጽ ቆጠራ የሚጀመርበት **(ድምፅ አሰጣጡ እንደተጠናቀቀ)** | ሕዳር 10 ቀን 2012 ዓ.ም. ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ |
| 15 | የህዝበ ውሳኔው የድምፅ ቆጠራ በድምፅ መስጫ ጣቢያው በይፋ የሚገለፅበት/በጣቢያው የሚለጠፍበት | ሕዳር 11 ቀን 2012 ዓ.ም. |
| 16 | የህዝብ ውሳኔ ውጤት ቦርዱ ጊዜያዊ ውጤት መግለጫ የሚሰጥበት | ህዳር 12 ቀን 2012ዓ.ም. |
| 17 | የህዝብ ውሳኔ ውጤት ሪፖርት በቦርዱ ፅድቆ ይፋዊ መግለጫ የሚሰጥበት | ሕዳር 17 ቀን 2012 ዓ.ም. |

***ሰንጠረዥ 2 ፡ የሲዳማ ህዝበ ውሳኔ ማስፈፀሚያ የጊዜ ሰሌዳ***

## *1.3 የምርጫ ሂደት የቅፃ ቅፆችና ቁሳቁሶች ዝግጅት*

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከዚህ በፊት በተካሄዱ ህዝበ ውሳኔዎች የተጠቀመባቸውን ቅፃ ቅፆችና ሰነዶችን በማሻሻል በቅፆቹ ላይ ውይይት አድርጎ የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት ለሲዳማ ህዝበ ውሳኔ የሚያገለግሉ ቅፃ ቅጾችን ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

### 1.3.1 የድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ የድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራ እና ውጤት አገላለፅ ቅፃ ቅፆች እና ሌሎች ህትመቶች

የድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ ቅፃቅፆች፣ የመክፈቻ እና መዝጊያ ቃለ ጉባኤዎች፣ ለመራጭነት የሚያበቁ ድምፅ ሰጪዎች የሚመዘገቡበት የመራጮች ካርድን ጨምሮ የድምፅ ሰጪዎች መዝገብ፣ በየዕለቱ የተመዘገበ ድምፅ ሰጪ፣ጥቅም ላይ የዋለ ካርድ፣አስፈፃሚዎችና ወኪሎች የሚተማመኑበት የዕለት መተማመኛ ቅፅና የተመዘገቡ ድምፅ ሰጪዎች ቁጥር ሪፖርት የሚደረግበት ቅጽን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም ለምርጫ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በመጠባበቂያነት የሚያገለግሉና በምርጫ ጣቢያ ለሚገኙ የተለያዩ አካላት የሚሰጡ ልዩ ልዩ መታወቂያዎችን ይጨምራል፡፡በአጠቃላይ ለድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ 17 (አስራ ሰባት) ዓይነት ሰነዶችና ቅፃ ቅፆች በጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በሌላ በኩል ለድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራ እና ውጤት አገላለፅ  አገልግሎት ላይ የዋሉት 16 (አስራ ስድስት) ዓይነት ቅፃ ቅፆች እና ሰነዶች ናቸው፡፡ ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የድምጽ ቆጠራ ውጤት ለዞን ማስተባበሪያ እና ለቦርዱ ማሳወቂያ ቅጽ፣ የምርጫ ጣቢያ  ውጤት ለሕዝብ ማሳወቂያ ፖስተር፣የድምፅ አሰጣጥ መክፈቻና መዝጊያ ቃለ ጉባኤ፣ የቆጠራ ማጠናቀቂያ ቃለጉባዔ ቅጽ፣ የድምፅ ቆጠራ ሂደት ማጠቃለያ ቅጽ፣ ለወኪል የሚሰጥ የቆጠራ ውጤት መተማመኛ እና  የድምጽ መቁጠሪያ ሰንጠረዥ  ቅጽ ናቸው፡

ለድምፅ  አሠጣጥ  ሂደት የታተሙ ዋና ዋና ቅፃ ቅፆችንና ሰነዶች (የድምፅ መቁጠሪያ ሠንጠረዥ፣ የምርጫ ጣቢያ የድምፅ ቆጠራ ውጤት ለህዝብ  ማሳወቂያ  ፖስተር፣ የድምፅ ቆጠራ ውጤት ለማስተባበሪያ ጽ/ቤት ማሳወቂያ፣ የድምፅ አሰጣጥና ሂደት መክፈቻ፣ ማጠናቀቂያ፣ የቆጠራ ሂደት ቃለ ጉባኤዎች)  በአጠቃላይ ብዛታቸው 2,619,840 (ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ አሥራ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ አርባ) የሆኑ ቅፆች በቦርዱ ማ/ቤት ታትመዋል፡፡

ለድምጽ መስጫ ወረቀት በጨረታ ህትመቱ በብራና ማተሚያ ቤት የተከናወነ ሲሆን በአጠቃላይ ለህዝበ ውሳኔው የታተመው የድምፅ መስጫ ወረቀት ብዛት በቁጥር 2,670,000 (ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ሺህ) ሲሆን የድምፅ መስጫ ቀን ፖስተር ብዛት ደግሞ 8,500 (ስምንት ሺህ አምስት መቶ) ነው።

በአጠቃላይ ለመራጮች ምዝገባ እና ለድምፅ አሰጣጥ ሂደት በቦርዱ እና በውጪ ማተሚያ ቤት የታተሙ የቅፃ ቅፅ ዓይነት 23 (ሃያ ሶሰት) ሲሆኑ አጠቃላይ ብዛቱ 5,298,340 (አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ ሶስት መቶ አርባ) ነው።

በተጨማሪም በኢንተርናሽናል ፋውንዴሽንስ ፎር ኢሌክቶራል ሲስተምስ (IFES) ድጋፍ የድምጽ መስጫ ፖስተር ህትመት መጠኑ A1 ብዛቱ 1700 (አንድ ሺህ ሰባት መቶ) እና የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች ማኑዋል ብዛቱ 5145 (አምስት ሺህ አንድ መቶ አርባ አምስት) በጥራዝ ታትሞ በስራ ላይ ውሏል።

### 1.3.2 የቁሳቁሶች ዝግጅት

ለድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ እና ለድምጽ አሰጣጥ ቆጠራ እና ውጤት አገላለፅ የሚያስፈልጉ የቁሳቁሶች ዝግጅትም ተደርጓል። በዚህም መሰረት አገልግሎት ላይ የዋሉት ቁሳቁሶች፤የድምፅ መስጫ ሳጥን፣ እስክሪብቶ፣ መርገጫ፣ ልዩ ማህተም፣ የምርጫ ማረጋገጫ ቀለም፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን መቆለፊያ ቁልፎች፣ መቀስ፣ ፖስታ፣ ኡሁ (ማጣበቂያ) ፣ባትሪ፣ የምርጫ ጣቢያ ቢሮ መቆለፊያ ቁልፍ እና የመሳሰሉትን በጨረታ ግዢ እና በአጋር ድርጅቶች ድጋፍ በስራ ላይ ውለዋል።

### 1.3.3 የድምፅ መስጫ ሣጥን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከተቋቋመበት ጊዜ ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ ፣አምስት(5) የጠቅላላ ምርጫዎች፣አራት (4) የአካባቢ ምርጫዎች እና በተለያዩ ቦታዎች የተከናወኑ ህዝበ ውሳኔዎች ላይ ይጠቀምበት የነበረው ኮሮጆ በሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ በአዲስ መልክ ተቀይሮ በምርጫ እና የፓለቲካ ፓርቲዎች አዋጅ 1162/2011 መሰረት ለመጀመሪያ ጊዜ ግልፅ የድምፅ መስጫ ሳጥን (Transparent Ballot Box) ተጠቅሟል። ይህም ከዚህ በፊት ከፍተኛ ቅሬታ ሲነሳበት የነበረውን ሙሉ ለሙሉ የተሸፈነ የኮሮጆን አሰራር አስወግዷል።



*ምስል-1፡ ግልጽ የድምጽ መስጫ ሳጥን*

## *1.4 ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይቶችን ማድረግ*

ቦርዱ የህዝበ ውሳኔው በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና በዋናነት የሚመለከታቸውን የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መንግስት፣የሲዳማ ዞን አስተዳደር፣የሀዋሳ ከተማ እና የፌደራል ፖሊስ፣የክልሉ እና ከዞኑ የጸጥታ ሀይሎች እንዲሁም ከአገር መከላከያ ሰራዊት ጋር በተለያዩ ጊዜያት የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ውይይቶችን አካሂዷል። የውይይቱ ዋና ዋና ሀሳቦችም የሚከተሉት ናቸዉ፡

- የምርጫ አስፈጻሚዎች አመላመል መስፈርቶች እና ቦርዱ የሚከተላቸው አካሄዶች፣
- በቦርዱ የተዘጋጀውን የህዝበ ውሳኔ አፈጻጸም መመሪያ፣
- በህዝበ ውሳኔው ላይ ሁለቱ ወገኖች የሚመርጡት የመወዳደሪያ ምልክት፣
- በቦርዱ የተዘጋጀው የህዝበ ውሳኔ አፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ
- የምርጫ ጸጥታ እና ደህንነት አስተዳደር
- የምርጫ ደህንነት እቅድ
- የሁለቱ ወገን ተወካዮች አሰያየም እና
- ለህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ማረፊያ ቦታ፣የመስተንግዶ እና ደህንነት ሁኔታ

በሚመለከቱ አጀንዳዎች ላይ ተደጋጋሚ ውይይቶች አድርጓል።

### 1.4.1 ወደ ሀዋሳ የቴክኒክ ቡድን መላክ

ቦርዱ ህዝበ ውሳኔውን ከማከናወኑ በፊት ህዝበ ውሳኔው በምርጫ ህጉና በተገቢው ሁኔታ ማከናወን እንዲቻል እና ለምርጫ አስፈጻሚዎች ከፀጥታ፣ ማረፊያ ቦታ፣ ከሎጀስቲከስ እና አቅርቦት አንፃር ያለውን ዝግጁነት የሚያረጋግጥ ቴክኒክ ቡድን ወደ ዞኑ ልኮ መረጃ አሰባስቧል፡፡

ቡድኑ ከክልሉ መንግስት፣ከሲዳማ ዞን አመራሮች፣ ከ 3 የወረዳ አስተዳደሮችና ከ3 ከተማ አስተዳደር አመራሮች ጋር በመወያየት ለህዝበ ውሳኔው አፈፃፀም የሚያስችል በሰላምና ፀጥታ ጉዳይ፣ በሎጅስቲክስ ጉዳይ እና የጸጥታ ችግር ጋር የተያያዘ የተለየ ችግር ሊኖርባቸው የሚችልባቸው ወረዳዎችን አስመልክቶ ውይይት አከናውኗል፡፡

### 1.4.2 ከደ/ብ/ብ/ሕ ክልል፣ ከሲዳማ ዞን እና ከጸጥታ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫውን በሚያስፈጽምበት ወቅት፣ ከደቡብ ክልል ምክር ቤት አመራር አካላት ጋር በቅርበት የሰራ ሲሆን በክልሉ ጸጥታ ጉዳዮች ላይ፣ በምርጫ ምልክቶች መረጣ ላይ፣ በበጀት ላይ አንዲሁም ለህዝበ ውሳኔው ከሚደረጉ ዝግጅቶች በክልሉ እና በዞኑ በኩል ስለሚጠበቁ ሃላፊነቶች ሰፊ ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ በዚህም መሰረት ቦርዱ እንዲዘጋጁ የጠየቃቸው የህግ ማእቀፍ ዝግጅት፣ የክልሉም የዞኑም ዋና ከተማ ሃዋሳን አስመልክቶ ውሳኔ ማሳለፍን የመሳሰሉ እና ለህዝበውሳኔው ሰላማዊነት ትልቅ ሚና ያላቸው ዝግጅቶች እንዲከናወኑ ተደርገዋል፡፡ ከዚያም በተጨማሪ በክልሉ መስተዳድር ጽ/ቤት ህዝበ ውሳኔውን ከሚያስተባብረው የፕሮጀክት ጽኅፈት ቤት ጋር የተቀናጁ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ውይይቶቹ በቦርዱ ዋና መስሪያ ቤት በኋላም ቦርዱ በጊዜያዊነት በሃዋሳ በአቋቋመው ጽ/ቤት የተከናወኑ ሲሆን ሁሉም ውይይቶች በቃለጉባኤ ተይዘዋል፡፡

## *1.5 የህዝበ ውሳኔ ማስፈፀሚያ ማንዋል ማዘጋጀት*

የሲዳማ በክልልነት የመደራጀት ህዝበ ውሳኔ በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ከምርጫ ህጉ በተጨማሪ ዘርዘር ያለ በህዝበ ውሳኔ አፈፃፀሙ ሂደት ላይ በግልፅ የሚያብራራ ማኑዋል የተዘጋጀ ሲሆን የማኑዋሉ ዋና ዋና ይዘቶችም የምርጫ አስፈጻሚዎች አመላመል፣በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያስችሉ መስፈርቶች፣የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ናቸው፡፡ ይህን ማኑዋል መሰረት በማድረግ ለምርጫ አስፈጻሚዎች የህዝበ ውሳኔ

ማስፈፀሚያ ማብራሪያ ተዘጋጅቶ ስልጠናም እንዲወስዱ እና በምርጫ አፈጻጸም ወቅት እለት በእለት እያጣቀሱ እንዲሰሩ በየምርጫ ጣቢያቸዉ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡

## *1.6 የሲዳማ ህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎችን መቅጠር፣ መመልመል እና ማደራጀት*

ቦርዱ በአዲስ መልክ የምርጫ አስፈጻሚዎችን በመመልመል አሰልጥኖ አሰማርቷል፡፡ የአስፈጻሚዎች ምልመላም ማስታወቂያ በማውጣት፣ከኦሮሚያ እና ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮዎች፣ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ መስፈርቱን የሚያሟሉ የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎችን በመምረጥ ህዝበ ውሳኔው እንዲፈጸም አድርጓል፡፡

### 1.6.1 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች የመምረጫ መስፈርቶች

- ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ የሆኑ፣
- የትምህርት ዝግጅታቸው በማንኛውም የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው፣
- የአዲስ አበባ እና የዙሪያው ነዋሪ የሆኑ፣
- ለህዝበ ውሳኔው በገጠር ቀበሌዎች ተንቀሳቅሰው መስራት የሚችሉ፣
- በማስፈፀም ልምድ ያላቸው እና
- ዕድሜያቸው ከ20 እስከ 50 ዓመት የሆኑ ከሁለቱም ፆታ የተውጣጡ የሚሉ ነበሩ፡፡

### 1.6.2 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ምዝገባ እና አመራረጥ

የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ በሰስት አይነት የአመራረጥ ዘዴ ተከናውኗል፡፡ የመጀመሪያው ልምድ ያላቸውን ምርጫ አስፈፃሚዎች ከአዲስ አበባ እና አዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ ወረዳዎች እንዲመዘገቡ የተደረገ ሲሆን በዚህም መሰረት 494 (አራት መቶ ዘጠና አራት) የምርጫ አስፈፃሚዎች ተመዝግበዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 980 (ዘጠኝ መቶ ሰማንያ) ፣ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 1600 (አንድ ሺህ ስድስት መቶ) እንዲሁም ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ 480 (አራት መቶ ሰማንያ) መስፈርቱን የሚያሟሉ የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ዝርዝር እንዲልኩ ተደርጓል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ማስታወቂያ በማውጣት እና በቴሌቪዥን በማስነገር በጊዜያዊነት 5436 (አምስት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ ስድስት) የአስፈጻሚዎች ምዝገባ የተካሄደ ሲሆን በድምሩ 8990 (ስምነት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና) አስፈፃሚዎች ለሲዳማ ህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚነት ተመዝግበዋል።

የምርጫ አስፈጻሚዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀ በኋላ በአጠቃላይ ከተመዘገቡት 8990 (ሰምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና) የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ውስጥ 5902 (አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሁለት) መስፈርቱን የሚያሟሉ እና የማስፈጸም ተግባሩን የመወጣት ብቃት ያላቸው ናቸው ተብሎ ታምኖበት ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።

### 1.6.3 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች መረጃ ማደራጀት እና ምደባ

የምርጫ አስፈጻሚዎች ምደባ በዘመናዊ አሰራር፤ በሁሉም የሲዳማ ዞን የሚገኙ ወረዳዎችና ምርጫ ጣቢያዎች ላይ ያለአድልዎ ለመመደብ የኮምፒዩተር አፕልኬሽን ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የተለያዩ የመመልመያ መስፈርቶችን ከግምት ዉሰጥ በማስገባት ተከናዉኗል፤ ከመስፈርቶቹም መካከል፣ሴቶችን ከተማ ላይ የመመደብ እና ለሴቶች እና ለአካል ጉዳተኞች የማይመቹ አካባቢዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት፣ ልምድ ያላቸው እና የሌላቸውን ተቀላቅለው እንዲመደቡ ማድረግ ይገኙበታል።

በተመሳሳይ መልኩ የወረዳ ክላስተር ምርጫ አስተባባሪዎች ምደባ ስልጠናውን ከወሰዱ የምርጫ አስፈጻሚዎች መካከል ከዚህ በፊት በምርጫ ማስተባበር ልምድ ያላቸውን የመምረጥ፣ለምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች ስልጠና ከሰጡ የቦርዱ ባለሙያዎች እና በስልጠናው ከተካፈሉ የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ሰራተኞች መካከል በስልጠናው ላይ ባሳዩት ተሳትፎ እና በመስሪያ ቤታቸው ያላቸውን ሃላፊነት ከግምት ዉስጥ በማስገባት የክላስተር አስተባባሪዎችን መመልመል ተችሏል።

በዚህም መሰረት በ2012 ዓ.ም በተካሄደው የሲዳማ የክልልነት መደራጀት ህዝበ ውሳኔ በ**15 (አስራ አምስት)** ወረዳ ክላስተር ማስተባበሪያዎች፤**32 (ሰላሳ ሁለት)** አስተባባሪዎች እና በ**1692 (አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት)** መደበኛ ምርጫ ጣቢያዎች እና **በ169 (አንድ መቶ ስልሳ ዘጠኝ)** ንዑስ ምርጫ ጣቢያዎች ተጠባባቂ ምርጫ አሰፈፃሚዎችን ጨምሮ **5902 (አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሁለት)** የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች ተመልምለው ህዝበ ውሳኔውን እንዲያስፈጽሙ ተደርጓል።

| ተ/ቁ | የወረዳ ማስተባበሪያ ስም | የወረዳ አስተባባሪ ብዛት | የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚ ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ሀዋሳ ከተማና ዙሪያ | 3 | 806 |
| 2 | ሸበዲኖ፣ለኩ | 3 | 688 |
| 3 | ቦርቻ፣ | 2 | 405 |
| 4 | አለታ ወንዶ | 2 | 324 |
| 5 | በንሳ፣ጨቤ፣ቡራ፣ | 2 | 499 |
| 6 | ቦና ዙሪያና ቡርሳ | 2 | 346 |
| 7 | አርቤጎና፣ሸፋሞ | 2 | 267 |
| 8 | አሮሬሳ እና ሆኮ | 2 | 287 |
| 9 | ሁላ፣ጭሮኒ፣ጠጥቻ | 2 | 270 |
| 10 | ይርጋለም፣ዳሌ | 2 | 662 |
| 11 | አለታጭኮ | 2 | 285 |
| 12 | ደራ፣ኢትልቾ | 2 | 293 |
| 13 | ጭሬና ዳኤላ | 2 | 177 |
| 14 | ሉካ አባያ | 2 | 211 |
| 15 | ወንዶገነት | 2 | 382 |
| | ድምር | 32 | 5902 |

***ሰንጠረዥ 3፡የተመለመሉ የምርጫ አስፈጻሚዎች ብዛት በወረዳ ማስተባበሪያ***

## *1.7 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ስልጠና*

ቦርዱ የህዝበ ውሳኔ አስፈፃሚዎች ስለህዝበ ውሳኔ እውቀት እንዲኖራቸው እና ስራቸውን በአግባቡ እንዲወጡ በማሰብ የአሰልጣኞች ስልጠና ለሁለት ቀናት እና ለእያንዳንዱ የምርጫ አስፈጻሚ የአፈጻጸም ስራ የሚረዳ የአንድ ቀን መሰረታዊ ስልጠና ሰጥቷል፡፡

### 1.7.1 የአሰልጣኞች ስልጠና

ከቦርዱ ለተመረጡ ባለሙያዎች እና ከተለያዩ የሲቪክ ማህበራት በስልጠና ላይ ልምድ ያላቸውን ባለሞያዎች በመምረጥ በህዝበ ውሳኔ አፈፃፀም ዙሪያ ለ29 (ሐያ ዘጠኝ) አሰልጣኞች በተግባር የተደገፈ የአሰልጣኞች ስልጠና በቦርድ አባላት፣በህግ ባለሙያዎች እና በቦርዱ ከፍተኛ የምርጫ ባለሙያዎች ለሁለት ቀን ተሰጥቷል፡

### 1.7.2 የህዝበ ውሳኔ የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች ስልጠና

ለምርጫ ጣቢያ የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች የአስልጠኞች ስልጠና በወሰዱ አስልጣኞች ለ5 ቀናት በ20 (ሐያ) ቡድን በመከፋፈል ስልጠና እንዲሰጣቸውና ወጥ የሆነ የስልጠና ማኑዋል በማዘጋጀት ለሰልጣኞች እንዲደርሳቸው ተደርጓል።

በስልጠናው የተካተቱት ርእሰ ጉዳዮች የህግ ማዕቀፍ፣በመራጮች ምዝገባ፣ በቅሬታ አቀራረብና አፈታት፣ በድምፅ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለፅ፣ በሰነዶች አጠቃቀምና አሞላል ሲሆኑ የተግባር ልምምድም እንዲኖር ተደርጓል። በአጠቃላይ ስልጠናውን የሰጡ አሰልጣኖች 22 (ሐያ ሁለት) ወንድ  እና 7 (ሰባት) ሴት በድምሩ 29 (ሀያ ዘጠኝ አሰልጣኖች) ሲሆኑ በአጠቃላይ ስልጠናውን የተካፈሉ የህዝበ ውሳኔው የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች 5902 (አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሁለት) ናቸው።



**ምስል 2፡ ለህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ስልጠና ሲሰጥ**

## *1.8 የአስፈፃሚዎች ምደባና ስምሪት*

የሕዝበ ውሣኔ አስፈፃሚዎች ከአዲስ አበባ ወደ ተመደቡበት ወረዳዎች እና ምርጫ ጣቢያዎች ከመንቀሳቀሳቸው በፊት የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚነት መታወቂያ የተሰጣቸው ሲሆን ሃላፊነትና ግዴታዎቻቸውን አስመልክቶ ገለጻ ተሰጥቷቸዋል። 106 (አንድ መቶ ስድስት) አውቶቡሶች ከአዲስ አበባ ወደ ምርጫ ወረዳዎች የሚሄዱበት አድራሻ በአውቶቡሶች ላይ በመለጠፍ 5902 (አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሁለት) የምርጫ አስፈፃሚዎችን አጓጉዘዋል። በስምሪቱ ወቅት ባጋጠመ ችግር ሃዋሳ ከተማ ያደሩ አስፈጻሚዎችንም በሚቀጥለው ቀን ወደተመደቡበት ጣቢያ በፍጥነት የማጓጓዝ ስራ ተሰርቷል። ሂደቱ በታቀደለት ሰአት ባይጠናቀቅም ለወደፊት የስምሪት ስራ ትልቅ ትምህርት የተገኘበት ነበር።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የምርጫ ወቅት ክንውን

### *2.1 የህዝበ ውሳኔ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ድልድል እና ስርጭት*

ለሲዳማ ህዝበ ውሳኔ ማስፈፀሚያ የሚያገለግሉ ሰነዶችና ቁሳቁሶችን በማደራጀት፣በተገቢው ቁጥር እና ስብጥር ለድምጽ ሰጪዎች ምዝገባ ሂደት እና ለድምጽ አሰጣጥ ሂደት በመደልደል በሲዳማ ዞን ለሚገኙ ወረዳዎችና ማስተባበሪያ ማዕከላት አሰራጭቷል።

በዚሁ መሰረት ለምዝገባው ሂደት የሚያገለግሉ ቅጻ ቅጾችና ተያያዥ ሰነዶች መታሸግ በሚገባቸው አይነት እና ቁጥር በቼክ ሊስት ተረጋግጦ፣ በአድራሻቸው ተዘጋጅቶ ለ1692 (አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት) መደበኛና 169 (አንድ መቶ ስልሳ ዘጠኝ) ንዑስ ጣቢያዎች እንዲዘጋጅ ተደርጓል። ለድምጽ አሰጣጥ ሂደት የሚያገለልሉ የተለያዩ ሰነዶችና ቁሳቁሶች እንዲሟሉ በማድረግ ለ1692 መደበኛ እና 169 ንዑስ ምርጫ ጣቢያዎችና ለ15 ማስተባበሪያ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን የማከማቸት፣ የመቁጠር፣ የማሰባጠር፣ የማሸግ እና የመደልደል ስራ ተከናውኗል።

ለምርጫ ማስፈፀሚያ ቁሳቁሶች ማለትም የድምፅ መስጫ ሳጥን 2000፣ የኮሮጆ ቁልፍ 8,000፣ መቀስ 2,000፣ የማሕተም መርገጫ 4,000፣ የማሕተም ቀለም 4,000፣ እስክሪብቶ 6,000፣ A4 ፖስታ 4,000፣ A5 ፖስታ 4,000፣ ልዩ ማህተም 2,000፣ የእጅ ባትሪ 2000 እና የምርጫ ጣቢያ በር ቁልፍ 2000 ለድምጽ መስጫ ቀን ጥቅም ላይ ውሏል።



*ምስል 3፡ የድምፅ መስጫ ወረቀት፣ቅፃቅፆችና ቁሳቁስ ሲደለደል*

## 2.2 የድምጽ መስጫ ወረቀት እና ፖስተር ዝግጅት

በሰባት ቀን ውስጥ በየምርጫ ጣቢያ የተመዘገበ መራጭ ቁጥርን መረጃ በማጠናቀር እና መሰረት በማድረግ ለገጠር እና ለከተማ ወረዳዎች 12 እና 13 በመቶ በመጨመር የድምጽ መስጫ ወረቀት ህትመት ተከናውኗል። ለሲዳማ ህዝበ ውሳኔ 2,670,000 (ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ሺህ) የድምፅ መስጫ ወረቀት እና ፖስተሮች፤ ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች ታትመው ተሰራጭተዋል።

ለስርጭቱም የተለያዩ የትራንስፖርት መገልገያዎች ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም የሃገር መከላከያ ሰራዊት ተሽከርካሪዎች፣ የጽ/ቤቱ የመስክ መኪኖች፣ በኪራይ የመጡ የጭነት መኪናዎች እና የጋማ ከብት በአገልግሎት ላይ ዉለዋል። የድምጽ መስጫ ሰነዶች ስርጭቱ በፌደራል ፖሊስ፣በሀገር መከላከያ ሀይል፣ በደቡብ ክልል መንግስት ሰላምና ጸጥታ ቢሮ፣በዞኑ ፖሊስ እጀባ ተደርጎለታል።



*ምስል 4፡ ለህዝበ ውሳኔ የሰነድ እና ቁሳቁስ ስርጭት የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች*

## 2.3 የመራጮች ምዝገባ

በ2012 ዓ.ም በተካሄደው የሲዳማ የክልልነት ጥያቄ ህዝበ ውሳኔ ለድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ ቦርዱ ባወጣው የምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሠሌዳ መሠረት የመራጮች ምዝገባ ከጥቅምት 27 እስከ ህዳር 6 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ ለ10 ቀናት በሲዳማ ዞን በሚገኙ እና በተቋቋሙ 1692 (አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት) የምርጫ

ጣቢያዎች ተከናውኗል፡፡በቁሳቁስ ስርጭት መዘገየት የተነሳ የመራጮች ምዝገባ ከታቀደለት ቀን አንድ ቀን ዘግይቶ ተጀምሯል፡፡ የህዝቡ ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ የመራጮች ካርድ እጥረት ባጋጠማቸው ወረዳዎች እና ምርጫ ጣቢያዎች 302,000 ተጨማሪ የመራጮች ካርድ እና መዝገብ ተከፋፍሏል፡፡

ከመራጮች ምዝገባ ጋር ተያይዞ በብላቴ ዙሪያ በ9 ምርጫ ጣቢያዎች ከኦሮሚያ የሀገር ሽማግሌዎች የመራጮች ምዝገባ ቢከናወን ለግጭት መነሻ ይሆናል በሚል ቅሬታ ቀርቦ ቦርዱ የሁለቱንም ወገን በማነጋገር የህዝቡ የመምረጥ መብትን ለማስጠበቅ ሁለቱም ወገን የተስማሙባቸውን ገለልተኛ የሆኑ ቦታዎች በመምረጥ ያለምንም የጸጥታ ችግር ምዝገባ ተከናውኗል፡፡

በተመሳሳይም በወንዶ ገነት ወረዳ በኤዶ ቀበሌ "ምርጫ ጣቢያ 1" ላይ ተመሳሳይ ቅሬታ ቀርቦ የመራጮች ምዝገባ በ"ምርጫ ጣቢያ 2" ላይ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

በምዝገባ ወቅት የአፈፃፀም ሂደቱን ክትትል በማድረግ ከተለያዩ የህብረተስብ ክፍሎች፣ከምርጫ አስፈፃሚዎች እና አስተባባሪዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች እና በህጉ መሰረት ላልተከናወኑ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ በመስጠት ማስተካከያ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

በዚህም መሰረት በ10 ቀናት በተካሄደው የመራጮች ምዝገባ በጠቅላላው በመራጭነት የተመዘገቡ ድምፅ ሰጪዎች ብዛት ወንድ 1,186,307 **(አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሰባት**) እና ሴት 1,118,270 **(አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ  አስራ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ**) በድምሩ 2,304,577 **(ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ሰባት**) ተመዝግቧል፡፡

## ***2.4 . የመራጮች ትምህርት እና መረጃ ተደራሽነት***

በምርጫ ወቅት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል አንደኛው የመራጮች ትምህርት እና መረጃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተለያዩ  መረጃዎች የመስጠት፣ የተዛቡ መረጃዎችን የማስተካከል እንዲሁም የመራጮች ትምህርትን በተለያዩ ስልቶች ለማድረስ ጥረቶችን አድርጓል፡፡

### 2.4.1 የህዝበ ውሳኔውን የጊዜ ሰሌዳዎች አስመልክቶ ለማህበረሰቡ መረጃ መስጠት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የህዝበ ውሳኔ የጊዜ ሰሌዳውን ከቦርዱ ማህበራዊ ሚዲያ በተጨማሪ በተለያዩ የህዝብ ሚዲያዎች እንዲተዋወቅ አድርጓል። በዚህም መሰረት በዋናነት የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፓሬሽን፣ ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፓሬሽን፣ ዋልታ ቲቪ፣ ደቡብ ቲቪና ሬዲዮ፣ ሲዳማ ቲቪ በመተባበር ግዴታ መሰረት በቋሚነት መረጃ እንዲያስተላልፉ ተደርጓል። ከነዚህ ሚዲያዎች በተጨማሪ በሲዳማ ዞን የሚገኙ የማህበረሰብ ሬዲዮኖች መረጃዎችን እንዲሰራጩ ተደርጓል። መረጃዎቹ የመራጮች ምዝገባን እና መስፈርቶቹን፣ ደምጽ አሰጣጥ ሂደትን እና በሰላማዊ መንገድ ምርጫው ላይ መሳተፍን የጨመሩ ሲሆን የመራጮች ምዝገባ በሚካሄድበት ጊዜ በሙሉ እንዲሁም የድምፅ መስጫ ቀን ድረስ የተለያዩ መረጃዎችን በቀን ሶስት ጊዜ ለማህረሰቡ እንዲቀርብ ተደርጓል።

መራጮች መረጃ ለመስጠት ከተዘጋጀው መልእክት በተጨማሪ ሁለት የአኒሜሽን ቪዲዮዎች፣ በቦርዱ ሰብሳቢ የተዘጋጁ ስድስት የቪዲዮ መልእክቶች ተቀርጸው ከላይ በተጠቀሱት ሚዲያዎች እንዲቀርቡ ተደርጓል። መልእክቶቹ በሲዳምኛ ቋንቋ ተተርጉመው እንዲቀርቡም ጥረት ተደርጓል።

ስለህዝበ ውሳኔው የሚዲያ ተደራሽነትን ለመጨመር በየእለቱ ለሚዲያዎች መረጃዎችን የመስጠት እና ጥያቄዎችን የመመለስ ስራ ተከናውኗል። የምርጫ ውጤትን አስመልክቶም ጋዜጣዊ መግለጫ የተሰጠ ሲሆን መረጃዎችም በተቻለ ፍጥነት ለሚዲያ እንዲደርስ ተደርጓል።

### 2.4.2 የመራጮች መረጃና ጥቆማ መስጫ የስልክ መስመር

የመራጮችን የመረጃ ማግኘት እድል ለመጨመር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በቀጥታ በስልክ መስመር መረጃ ሲሰጥ ቆይቷል። የመራጮች ምዝገባ ወቅት ሁለት የስልክ መስመሮች በስራ ሰአት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ የቆዩ ሲሆን ድምጽ መስጫ ቀን ተጨማሪ አራት የስልክ መስመሮች ተጨምረው ለድምጽ ሰጪው እንዲሁም ለምርጫ አስፈጻሚዎች የመረጃ መስጫ መንገድ ሆነው አገልግለዋል።

በቀጥታ የስልክ መስመሮች በተገኙ መረጃዎች፣ የአሰራር ክፍተቶችን ለማስተካከል፣ የህግ ጥሰቶችን ለመከታተል አንዲሁም ለአስፈጻሚዎች መረጃ ለመስጠት ጠቃሚ ሆኗል። የስልክ ጥቆማዎችን በመጠቀም ከፍተኛ የመራጭ ሰልፍ ላለባቸው ቦታዎች የአስፈጻሚ እገዛ ለመላክ፣ ቁሳቁስ ለማሟላት እንዲሁም

ከመታወቂያ ጋር በተያያዘ ከህግ ውጪ የሰሩ ምርጫ ጣቢያዎችን ማስተካከል ተችሏል። የቀጥታ የስልክ መስመሮች ጥሪን ለሚቀበሉ ሰዎች የመረጃ ማጠናቀሪያ ቅጽ እና በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል። በስልክ መስመሩ ከሚሰጡ ጥቆማዎች በመነሳት የቦርዱ መረጃ አሰጣጥም የተሻሻለ ሲሆን በዚህም መሰረት መታወቂያን አስመልክቶ እንዲሁም ሌሎች የቦርዱን ስራዎች አስመልክቶ የተለያዩ መረጃዎችን ለማህበረሰቡ በተከታታይ ሲሰጥ ቆይቷል።

## *2.5 የምርጫ ጸጥታ እና ደህንነት*

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሲዳማ ህዝበ ውሳኔን በሰላማዊ መንገድ ለማስፈጸም ከፍተኛ ጥረትና ዝግጅት አድርጓል። በዚህም መሰረት የምርጫ ጸጥታ እና ደህንትን የሚያይ ከተለያዩ ፀጥታ አካላትና ማህበረሰብ ክፍሎች የተውጣጣ ኮሚቴ ተቋቁሞ ስራውን በሚገባ አስፈጽሟል። የአገር መከላከያ ሰራዊት፣ የደቡብ ክልል ጸጥታ እና ደህንነት፣ የክልሉ ፓሊስ እና የሲዳማ ዞን ጸጥታ እና ህግ አስፈጻሚ አካላት የተካተቱበት ኮሚቴ በህዝበውሳኔው ወቅት የሚፈጠሩ እና የጸጥታ ችግር ሊፈጠሩ የሚሉ ችግሮችን አስቀድሞ በመለየት ማህበረሰቡን በማነጋገር የምርጫውን ደህንነት አንዲጠበቅ አድርጓል። በሂደቱም ከማህበረሰብ ተወካዮች ጋር የተለያዩ ውይይቶች የተደረጉ ሲሆን፣ የምርጫ ጣቢያ ቦታዎችን በማህበረሰቡ ጥያቄ የመቀየር፣ እንዲሁም ግጭት ሊቀሰቅሱ የሚችሉ ችግሮችን ሪፖርት በመከተል እርምጃ በመውሰድ ምንም አይነት የጸጥታ ችግር ሳይፈጠር ህዝበ ውሳኔው ተጠናቋል።

## *2.6 የድምፅ መስጠት ሂደት*

ህዳር 10 ቀን 2012 ዓ.ም. በተካሄደው የሲዳማ ህዝበ ውሳኔ ለድምፅ አሰጣጥ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ ሂደት የሚያገለግሉ የድምጽ መስጫ ወረቀት፣ ፖስተሮች፣ሌሎች ሰነዶችን በማተም፣በጥንቃቄ በመቁጠር፣ የምርጫ ቁሳቁሶችን ጨምሮ የመደልደልና የማሰራጨት ስራ በተሳካ ሁኔታ ተከናውኗል።

ቦርዱ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በ15 የወረዳ ማስተባበሪያዎች በሚገኙ በ1692 መደበኛ ምርጫ ጣቢያዎች እና 169 በኃላ በተከፈቱ ንዑስ የምርጫ ጣቢያዎች ህዳር 10 ቀን 2012 ዓ.ም. በሕጉ መሠረት ከማለዳው 12፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 12፡00 ድረስ ሰላማዊ በሆነ መልኩ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ተከናውኗል ። በእለቱ ምንም አይነት የጸጥታ ችግር ሳያጋጥም የድምጽ መስጠት ሂደቱ ተጠናቋል።

### 2.6.1 ለተጨመሩ ምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚዎች ስምሪት

በድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ ወቅት ከ 1500 በላይ መራጭ የመዘገቡ እና በተጨማሪ መዝገብ የተጠቀሙ ምርጫ ጣቢያዎች በድምጽ መስጫው ቀን መጨናነቅን ለመቀነስ አዲስ የምርጫ ጣቢያ በመክፈት ተጨማሪ የሰው ሀይል እንዲመደብላቸው ተደርጓል።

### 2.6.2 የድምፅ አሰጣጥና ቆጠራ

በድምፅ መስጫው ቀን የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የስነሥርዓት አስከባሪዎች እና የምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች የተገኙ ሲሆን በወኪሎች በኩል ግን የአንድ ወገን ( የሲዳማ ክልልነት ጥያቄ ወኪሎች) ብቻ ተገኝተዋል።

መራጮች ከንጋቱ12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓት ድረስ በየተመዘገቡበት የምርጫ ጣቢያ በግንባር እየተገኙ ሰላማዊ በሆነ መልኩ ድምፃቸውን ሲሰጡ ውለዋል። በዘጠኝ የምርጫ ጣቢያዎች ረዥም ሰልፍ በመኖሩ ምክንያት የድምፅ አሰጣጡ እስከ ምሽቱ 1፡45 ድረስ ሊዘገይ ችሏል።

በዕለቱ የድምጽ መስጫ ወረቀት እጥረት ባጋጠመበት እና ተጨማሪ የድምጽ መስጫ ሳጥን ባስፈለገበት የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ላይ የሟሟላት ስራ ለማከናውን ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። የድምጽ መስጫው እለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አመራር አባላት በሃዋሳ ከተማ ቅኝት አከናውነዋል። ስራዎችንም አስተባብረዋል። የድምፅ አሰጣጡ ሂደት በብዙዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት በፊት ተጠናቋል። ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ላይ ምርጫ ጣቢያዎች ተዘግተው የቆጠራው ሂደት በይፋ ተጀምሯል። የድምፅ ቆጠራው ሂደት የወኪሎች እና የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የዓለም አቀፍ እና የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች ተገኝተውበታል።የውጤት ቆጠራን ቀድመው የጀመሩ የተወሰኑ ጣቢያዎች ተገኝተዋል።



*ምስል 7፡ ድምፅ ሲሰጥ*

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. ድህረ ምርጫ

### *3.1 ውጤት አገላለጽ*

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ሕግ መሠረት የድምፅ አሰጣጡ ሂደት እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ የድምፅ ቆጠራው በየምርጫ ጣቢያው የተካሄደ ሲሆን ውጤቱም በእለቱ ምርጫ ጣቢያዎች ላይ ለሕዝብ እንዲለጠፍ ተደርጓል። የድምፅ ቆጠራውን እና ማዳመሩ የተከናወነው በሚመለከታቸው የምርጫ ጣቢያ  የምርጫ አስፈፃሚዎች ሲሆን ሂደቱም ወኪሎች፣ የሀገር ውስጥ እና የዓለም አቀፍ ታዛቢዎች እና ሚዲያዎች የተገኙበት ነበር።

የወረዳ ክላስተር አስተባባሪዎች በምርጫ ጣቢያ የተሞላውን የምርጫውን ውጤት ቅፅ ይዘው እንዲመጡ በማድረግ ለዞን ማስተባበሪያ እንዲያስረክቡ ተደርጓል። ጊዜያዊ ውጤት ቦርዱ በምርጫ ሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ህዳር 13 ቀን 2012 ዓ.ም. በሀዋሳ ከተማ  ይፋ አድርጓል። በመጨረሻም ቦርዱ ባወጣው የምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሠሌዳ መሠረት አጠቃላይ የምርጫውን ውጤት ህዳር 24 ቀን 2012 ዓ.ም. ይፋ አድርጓል። ውጤቱም በዝርዝር በቦርዱ ፌስቡክ ገፅ እንዲለጠፍ ከመደረጉም በላይ ለተለያዩ ሚዲያዎች በመግለጫ እንዲደርሳቸው ተደርጓል።

### *3.2 በቦርዱ የጸደቀ የምርጫ ውጤት*

የአትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ውጤቱን በህግ እና በአለም አቀፍ ስታንዳርዶች በመጠቀም ከተመዘገበው መራጭ በላይ ድምፅ ተሰጥቶ የተገኘባቸው 127 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ ያለ ውጤት እንዲሰረዝ፣  በቆጠራ እና በድምር ስሌት ስህተት ከተገኘባቸው ጣቢያዎች መካከል የታየው ልዩነት 10 ድምፅ እና ከዚያ በታች የሆኑ ልዩነቶች ዋጋ እንዳላቸው ድምፅ እንዲቆጠሩ፣ ነገር ግን በ10 ድምፅ በላይ የድምር ልዩነት የተገኘባቸው ጣቢያዎች ውጤት እንዳይካተት ወስኗል። በዚህም መሠረት 37 ምርጫ ጣቢያዎች በከፍተኛ የድምርና የስሌት ስህተት የተነሳ ውጤታቸው ተሰርዟል።

በአጠቃላይ በማጠናቀቂያ ውጤቱ 164 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ ያሉ ውጤቶች ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ምክንያቶች የተነሳ እንዲሰረዙ የተደረገ ሲሆን 71 የምርጫ ጣቢያዎች ግን የድምር ልዮነቱ ከ10 ድምፅ በታች በመሆኑ ስህተት ቢኖራቸውም ውጤታቸው ዋጋ ኖሮት እንዲቀጥል ተደርጓል።

እንደዚህ ዓይነት የውጤት አለመጣጣም ከፍተኛ ውድድር ባለባቸው እንደ አገር አቀፍ ምርጫ ያሉ ውድድሮች ላይ ቢፈጠሩ የሚኖራቸውን ተጽእኖ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል በመረዳት ቦርዱ እነዚህ ችግሮች የተፈጠሩበትን ምክንያት የሚያጣራ የቴክኒክ ቡድን አቋቁሟል። የቴክኒክ ቡድኑ የማጣራት ውጤትን መሠረት አድርጎም ለቀጣዩ ምርጫ አስፈላጊውን የአቅም ግንባታ ስራዎችን፣ የአስፈጻሚዎች ስልጠና እና የምርጫ ሂደቱን የማሻሻል ስራዎችን የሚሰራ ይሆናል።

በዚህም መሰረት የህዝበ ውሳኔው የመጨረሻ ውጤት የሚከተለው ነው።

- **የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር - 2,304,577**
- **ድምፅ የሰጡ መራጮች ቁጥር - 2,279,022**
- **በመቶኛ - 98.8911 %**
- **ድምፅ ያልሰጡ መራጮች ቁጥር - 25,555**
- **በመቶኛ - 1.10888 %**

አጠቃላይ ውጤት

- **ዋጋ አልባ ድምፅ መስጫ ወረቀት - 16,624**
- **ለሻፌታ (ለሲዳማ በክልልነት መደራጀት ድምፅ የሰጡ) መራጮች ቁጥር - 1,984,283 በመቶኛ - 97.7**
- **ለጎጆ (በደቡብ ክልል ለመቆየት ድምፅ የሰጡ) መራጮች ቁጥር - 30,018 በመቶኛ - 1.478**
- **የተሰረዘ ድምፅ - 248,097**

## *3.3 በምርጫ ክትትል የተሰሩ ሥራዎች*

- የሕዝበ ውሣኔ ምርጫ አስፈፃሚዎች ስልጠናውን በአግባቡ መውሰዳቸው ክትትል ተደርጓል።
- ከአዲስ አበባ ወደ ወረዳዎች እና ከወረዳዎች እስከ ምርጫ ጣቢያ የሕዝበ ውሣኔ አስፈፃሚዎች በወቅቱ ያለምንም ፀጥታ ችግር መድረሳቸው ክትትል ተደርጓል።
- በተለያየ ምክንያት በምርጫ ጣቢያ ያልተመደቡ አስፈፃሚዎችን የመመደብ እና ከሃዋሳ ከተማና ሲዳማ ዞን አስተዳደር ጋር ትራንስፖርት በማመቻቸት እንዲሰማሩ የማድረግ እና መድረሳቸውን በተመለከተ የክትትል ስራ ተፈጽሟል።

- የድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ በሕጉ መሠረት እየተከናወነ ለመሆኑ በስልክ፣ በመስክ፣ በሆትላይን እና በተለያዩ ጥቆማዎች ላይ ክትትል የማድረግ ሥራ እና የእርምት ሥራ ተከናውኗል።
- እጥረት ባጋጠመባቸው ጣቢያዎች የድምፅ ሰጪዎች ካርድ እና በመጠባበቂያነት የተላከ የድምፅ መስጫ ወረቀት፣ የድምፅ መስጫ ሳጥን እና ሌሎች ቁሳቁሶች በየምርጫ ጣቢያው የማድረስ ሥራ ተከናውኗል።
- ሁሉም የምርጫ አስፈፃሚዎች የውሎ አበል ክፍያ ማግኘታቸውን ክትትል የተደረገ ሲሆን ለዘገየባቸው ምርጫ አስፈፃሚዎች ክትትል በማድረግ ከፋዮች በድጋሚ ሄደው ክፍያ እንዲፈጽሙ ተደርጓል።
- ሕመም ያጋጠማቸው የምርጫ አስፈፃሚዎችን ሕክምና በአቅራቢያቸው በሚገኙ ወረዳዎች የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸቱን የማረጋገጥ ስራ ተከናውኗል ።
- የምርጫ ጣቢያ ውጤት ቆጠራው እንደተጠናቀቀ ለሕዝብ መለጠፉን ክትትል የማድረግ ሥራ ተከናውኗል።
- የወረዳ አስተባባሪዎች ከምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች የምርጫ ውጤት በመረከብ ዞን ማዕከል ድረስ እንዲያመጡ የክትትል ስራ ተከናውኗል።
- የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች ክፍያ ማግኘታቸው እየተረጋገጠ በተዘጋጀላቸው አውቶብስ ከወረዳ ማስተባበሪያ ወደ አዲስ አበባ አጃቢ በማዘጋጀት መሄዳቸው ተረጋግጧል።

## *3.4 የሲዳማ ህዝበ ውሳኔ የበጀት አጠቃቀም*

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ህዝበ ውሳኔን የማስፈጸሚያ በጀት ብር 75 ሚሊዮን ብር ወደ ምርጫ ቦርድ የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ሲሆን፤ ህዳር 10 ቀን 2012 ዓ.ም. በተደረገው ህዝበ ውሳኔ አጠቃላይ ስልሳ ዘጠኝ ሚልዮን ስድስት መቶ ሰባ አራት ሺ ሰባት መቶ ሰላሳ ሁለት ብር ከአርባ ሁለት ሳንቲም (**69,674,732.42)** ህዝበ ውሳኔውን ለማስፈጸም ጥቅም ላይ ውሏል። ዋና ዋናዎቹ ወጪዎች፣ የህትመት፣ የአስፈጻሚዎች አበል ክፍያ እና የእቃዎች ግዥ ሲሆን ዝርዝሩ የሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ይገኛል። በቀረበው ቢጋር (TOR) መሠረት ብር 133,739.64 ለሠነድ ማሰባሰቢያ ወደፊት የሚወጣ ወጪ ሲሆን ከስር በተገለጸው የበጀት አጠቃቀም ሪፓርት የማሰባሰብ ወጪ ሙሉ በሙሉ አልተካተተም።

| ተ.ቁ | የወጪው ዓይነት | የገንዘቡ መጠን |
|---|---|---|
| **1** | **ለጽ/መሳሪያ ግዥ** | **20,469.33** |
| **2** | **ለህትመት** | **2,439,097.00** |
| **3** | **ነዳጅ** | **233,254.49** |
| **4** | **ልዩ ልዩ መሳሪያዎች** | **200.00** |
| **5** | **የውሎ አበል** | **49,172,522.00** |
| **6** | **ትራንስፖርት** | **6,954,374.02** |
| **7** | **መስተንግዶ** | **62,215.86** |
| **8** | **ለማስታወቂያ** | **261,000.50** |
| **9** | **ማስጫኛ** | **17,612.50** |
| **10** | **አገልግሎት ክፍያ** | **5,092.98** |
| **11** | **የስልክ (የሞባይል) ካርድ** | **363,042.50** |
| **12** | **ቋሚ እቃ ግዥ** | **10,012,111.60** |
| **13** | **ውሎ አበል እና ለነዳጅ *** | **133,739.64** |
| | ጠቅላላ ወጪ | **69,674,732.42** |

***ሰንጠረዥ- 4:የበጀት አጠቃቀም ማጠቃለያ***

# ምዕራፍ አራት

## 4. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ከህዝበ ውሳኔው የተገኙ ትምህርቶች

በሲዳማ የክልልነት ጥያቄ ህዝበ ውሳኔ በስኬት የተጠናቀቀ ቢሆንም በስራው ሂደት የነበሩ ጠንካራ ጎኖች፣ ያጋጠሙ ችግሮች ለወደፊቱ ቦርዱ ለሚያከናውናቸው ስራዎች ከፍተኛ ትምህርት ሰጥቷል። በሂደቱም ሲቪል ማህበራት ምርጫውን የታዘቡ ሲሆን ሚዲያዎችም ሂደቱን በመዘገብ የቦርዱን ስራ ግልጽነት ለማረጋገጥ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

### 4.1 በህዝበ ውሳኔው የሲቪል ማህበራትና የሚዲያ ተሳትፎ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሲዳማ ህዝበ ውሳኔን በሚያስፈጽምበት ወቅት ሲቪል ማህበራት ህዝበ ውሳኔውን እንዲታዘቡ የቅድመ ዝግጅት ስራዎቻቸውን በማገዝ፣ እውቅና በመስጠት እንዲሁም በድምጽ መስጫ ቀን ስምሪታቸውን በማስተባበር የህዝበ ውሳኔውን ተአማኒነት ገለልተኛ ተቋማት እንዲታዘቡት አድርጓል። ከአገር በቀል የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች ጥምረት በተጨማሪ ከአሜሪካን መንግስት የተወከሉ ታዛቢዎች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የተሰማሩ ታዛቢዎች የምርጫ ሂደቱን ታዝበዋል፡ ፡ ከሲቪል ማህበራት በተጨማሪ  የተለያዩ ሚዲያዎችን የወከሉ ጋዜጠኞች የህዝበ ውሳኔ ሂደቱን እንዲከታተሉ እና እንዲዘግቡ የእውቅና ፍቃድ ሰጥቷል።

#### 4.1.1 ሲቪል ማህበራት እና የህዝበ ውሳኔው መታዘብ ሂደት -

“የአትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ጥምረት ለምርጫ” የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በማስተባበር እና በመምራት ህዳር 10 ቀን 2012 ዓ.ም. የተካሄደውን የሲዳማ ህዝበ ውሳኔን የታዘቡ ሲሆን ከ60 ድርጅቶች የተውጣጡ፣ 178 ታዛቢዎች በቋሚና በተዘዋዋሪ ታዛቢነት ተሳትፈዋል። የሲቪል ማህበራት ጥምረቱ የትዝብት ውጤቱን ሪፓርት ያቀረበ ሲሆን በ16 ወረዳ የሚገኙ 147 የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ታዛቢዎች ተሰማርተዋል።

እነዚህ ታዛቢዎች የሲዳማ ሀዝበ ውሳኔ ከፍተኛ ቁጥር ያለው መራጭ ወጥቶ ያለምንም የጸጥታ ችግር ድምጹን የሰጠበት፤ በሰላም ተጀምሮ በሰላም የተጠናቀቀ ሲሆን በአብዛኛዎቹ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የተሠማሩ የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ሙያዊ ብቃት ማሳየታቸውን፤ በባለድርሻ አካላት መካከል ትብብር እና መናበብ ጠንካራ እንደነበር፤ አብዛኛዎቹ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ህግ በደነገገው ሰአት መከፈታቸውን፤ ህግ በደነገገው ሰአትም መዘጋታቸውን እንዲሁም ወዲያውኑ የድምጽ ቆጠራ መጀመሩን ፤

ውጤቶችም ወዲያውኑ መለጠፋቸውን፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጥምረት ታዛቢዎቹን ባሰማራባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለመታዘብ ችሏል፡፡ በሌላ በኩልም የታዛቢ ቡድኑ ቀላል በማይባሉ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በህግ ከተደነገገው ከ1500 በላይ ድምጽ ሰጭዎች መታየታቸው፤ህግ ከደነገገው ሰአት አስቀድመው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን የከፈቱ እንዲሁም በህግ ከተደነገገው ሰአት አስቀድመው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን የዘጉ፤ ጣት ላይ የሚቀባ ቀለም ያለቀባቸው፤ ድምጽ ሰጭዎች ደምጽ ከሰጡ በኋላ ጣታቸውን ቀለም ሣይቀቡ መሄድ፤ የድምጽ መስጫ ሳጥኖች መሙላት፤ ድምጽ ሰጭዎች ምን ላይ ምልከት እንዳለባቸው የሚነግሩ አልፎ ተርፎም ምልክት የሚያደርጉ ሰዎች እንደነበሩ ታዝቧል፡፡ የመታዘብ ሪፖርቱን እና ለወደፊቱ ሊከናወኑ የሚገባቸው ምክረ ሃሳቦችን ይፋ አድርገዋል፤ ለቦርዱ አቅርበዋል፡፡

### 4.1.2 የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የመታዘብ ሂደት

ኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን 20 አባላት ያሉት በዋና ኮሚሽነሩ የተመራ የሰብአዊ መብት ታዛቢ ቡድን የህዝበ ውሳኔው እለት ያሰማራ ሲሆን የክትትል ቡድኑ በምርጫው ቀን በ 5 የከተማ አስተዳደሮች እና 15 የገጠር ወረዳዎች ውስጥ 100 የምርጫ ጣቢያዎችን ተመልክቷል፡፡

የቅድመ-ምርጫ እና ምርጫው የተካሄደበት ዕለት ህዳር 10 ቀን 2012 ዓ.ም. በሰላም የተጠናቀቀ መሆኑን፤ የኢሰመኮ የሰብዓዊ መብት የክትትል ቡድን በምርጫው ቀን አነስተኛ ጉድለቶች ብቻ እንደነበሩ ሪፖርት አድርጓል ፡፡ በመራጮች ምዝገባ ወቅት እድሜያቸው ለምርጫ ያልደረሰ የሚመስሉ ነገር ግን መታወቂያ ያላቸው ወጣቶችን መመልከቱን እና ይህም ለምርጫ ቦርድ ሥራ ልዩ ተግዳሮት መሆኑን ኮሚሽኑ የገለጸ ሲሆን በሁሉም ደረጃ ያሉ የክልልና የፌዴራል ባለስልጣናት እና የብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ለምርጫው አስፈላጊ የሆነው የጸጥታና ደህንነት ሁኔታ እንዲፈጠር በጥሩ ሁኔታ መስራታቸውን አድንቋል፡

ኮሚሽኑ በሪፓርቱ እንደገለጸው አንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች አካባቢ የተወሰኑ የወጣት ቡድኖች ድምፅ ለመስጠት ለተሰለፉ ሰዎች የምርጫ ቅስቀሳ ሲያደርጉ ታይተዋል፡፡ ለአማራጩ የጎጆ ቡድን የምርጫ ቅስቀሳ በይፋ የተከለከለ ነገር ባይኖርም፣ በርካታ አስተያየት ሰጭዎች ለኢሰመኮ ታዛቢዎች እንደገለጹት፤ በሲዳማ የፖለቲካ ነባራዊ ሁኔታ አማራጩን ሐሳብ በይፋ ለመቀስቀስ ስጋት እና ፍራቻ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተጨናነቀ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ሰላማዊ ምርጫን ለማደራጀት እና ለማስፈጸም የተቀናጀ

ጥረት ያደረገ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ብቻ አነስተኛ የሥነ ሥርዓት ችግሮች ታይቷል ፡፡

### 4.1.3 ህዝበ ውሳኔውን የዘገቡ ሚዲያዎች

ሕዝበ ውሳኔውን ለመዘገብ የሚፈልጉ እና በኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን እውቅና ያላቸው ሚዲያዎች ጥያቄያቸውን ለቦርዱ እንዲያቀርቡ በወጣው ማስታወቂያ መሰረት ሚዲያዎች ጥያቄያቸውን በደብዳቤ እና በኢሜል ያቀረቡ ሲሆን በዚያ መሰረት የእውቅና ፍቃድን እንዲያገኙ ተደርጓል። በአጠቃላይ 76 ጋዜጠኞች የእውቅና መታወቂያ ተሰጥቷል። የህዝበ ውሳኔ ሂደቱም የመራጮች ምዝገባ መከፈትን አስመልክቶ፣ የመራጮች ምዝገባ ሂደትን እና መጠናቀቅን አስመልክቶ፣ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫዎች የተሰጡ ሲሆን ከዚያም በተጨማሪ በየእለቱ በቀጥታ የቴሌቪዥን እና የሬዲዮ ማብራሪያዎች ተሰጥተዋል። የህዝበ ውሳኔው ጊዜያዊ ውጤትም ይፋዊ ጋዜጣዊ መግለጫ የተሰጠ ሲሆን የመጨረሻው ውጤት ደግሞ ለሚዲያዎች የጽሁፍ ጋዜጣዊ መግለጫን በመላክ ይፋ ተደርጓል።

## *4.2* ከህዝበ ውሳኔው የተገኙ ዋና ዋና ትምህርቶች

## *4.2.1 የህዝበ ውሳኔው አጠቃላይ አፈጻጸም ላይ የተገኙ ዋና ዋና ትምህርቶች*

**<u>ጠንካራ ጎኖች</u>**

- በ5 ቀናት ውስጥ ቁጥሩ 5902 የሆነ ምርጫ አስፈጻሚ አሰልጥኖ ለህዝበ ውሳኔ አፈፃፀም ዝግጁ ማድረግ፣ የስልጠና ዝግጅት ማቴሪያሎች በተሟላ መልኩ መዘጋጀታቸው እና ለአስፈጻሚዎች መሰጠታቸው፣
- በየደረጃው በተደራጁ የፀጥታ መዋቅሮችን በማወያየት ራሱን የቻለ የደህንነት (security) እቅድ እንዲዘጋጅ ብሎም እንዲፈፀም በማድረግ፣ በማሰማራት ሕዝበ ውሣኔው ያለምንም ፀጥታ ችግር በሰላም መከናወኑ፣
- የቦርድ አመራር አባላት በቅርበት በሃዋሣ ከተማ በመገኘት የሕዝበ ውሣኔውን አፈፃፀም ክትትል ማድረጉ፣ የነበሩ ችግሮችና ቅሬታዎች በወቅቱ መፍታት መቻሉ፣
- በአጭር ጊዜ ውስጥ የምርጫ ቦርድ እና የአጋር ድርጅቶች የሰውሃይልና ሃብትን አሰባስበው ህዝበ ውሳኔውን በአጥጋቢ ሁኔታ መፈጸም መቻሉ
- የምዝገባ እና የድምጽ መስጫ ሰነዶች ስርጭት ሰህተቶችን በፍጥነት ማረም መቻሉ

- የድምጽ መስጫ ወረቀት ህትመትን በመራጮች ምዝገባ መረጃ መሰረት በማድረግ እንዲታተም እና በአጭር ጊዜ እንዲደርስ ማድረግ
- የሰነዶች ስርጭት ከነበረው የጊዜ ጥበት አንጻር በታቀደለት ወቅት እንዲደርስ መደረግ መቻሉ፣
- የ1692 መደበኛ ምርጫ ጣቢያዎች እና 169 ንዑስ ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጥ ሰነድና ቁሳቁስ በወቅቱ ለማድረስ 50 ተጨማሪ ጊዜያዊ ሠራተኞችን በ2 ቀን ቀጥሮ ወደ ሥራ አሰማርቶ ማሠራት መቻሉ እና በሁለት ቀን ብቻ ቆጥሮ፣ ደልድሎ በወቅቱ ማሠራጨቱ፣
- አጠቃላይ በህዝበውሳኔ አፈጻጸም ወቅት ከፍተኛ የሆነ ችግሮች ላይ ክትትል ማድረግና ቶሎ መፍትሄ በመስጠት( crisis management)  ከፍተኛ ክህሎት መኖሩ።

## ያጋጠሙ ችግሮች

- በሁሉም የምርጫ አፈፃጸም ተግባራት ላይ ከፍተኛ የጊዜ እጥረት መኖር፣
- የህዝበ ውሳኔው እቅድ ሲዘጋጅ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች የእቅዱ አካል አለመሆናቸው፣
- ለህዝበ ውሳኔው የሚያስፈልጉ መረጃዎች ጥራት አለመኖር፣
- ከ1500 በላይ መራጮ ላላቸው የምርጫ ጣቢያዎች ተጨማሪ ጣቢያችን የመክፈት አሰራር ዝግጅት አለመኖር፣
- የምርጫ አስፈጻሚዎች ቅጥር፤ምዝገባ፣መረጣ እና ስምሪት መረጃ አሰባሰብ በአግባቡ ያልታቀደ እና ያልተደራጀ  መሆን፣
- የምርጫ ጣቢያዎች አሰያየም እና ቦታ መረጃዎች የተምታቱ መሆናቸው፣
- የምርጫ ቁሳቁሶች እጥረት ( ድምጽ መስጫ ሳጥን መሙላት፣ ወረቀቶች ማነስ …የመሳሰሉት) በተለያዩ የምርጫው ሂደት መታየታቸው ፡፡

## የተገኙ ትምህርቶች እና ለወደፊቱ መደረግ ያለበት

- እቅዶች ላይ ሁሉም የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እንዲካተቱ ማድረግ
- የእቃዎች ዝግጅት፣ድልድል እና ስርጭትን አስመልክቶ ግልጽ የአሰራር ሂደት ማንዋል ማዘጋጀት
- የምርጫ ኦፕሬሽን ለመምራት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመቅረፍ ከፍተኛ የሰራተኛ አቅም ግንባታ ማከናወን
- የምርጫ ጣቢያዎች ስያሜ ስርአት ማውጣት

- ለኦፕሬሽን ስራ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ቀድሞ ማጠናቀርና ኦፕሬሽንን በዚያ መረጃ መሰረት አድርጎ መምራት
- የተለየ የመረጃ እና የዳታ አስተዳደር ስርአት መዘርጋት

## *4.2.2 የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላ*

***<u>ያጋጠሙ ችግሮች</u>***

- በቅጥር የተመዘገቡ አስፈፃሚዎች ምዝገባ በዲጂታል መልኩ አለመከናወን ከፍተኛ የዳታ ጥራት ችግር ማስከተሉ፣
- 5902 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎችን ለመመዝገብ የሚያስችል የሰው ሀይል እና ዘመናዊ አደረጃጀት አለመኖር፤
- በምርጫ አስፈፃሚዎች ስልጠና እና ጥሪ በተጠና እና በታቀደ መልኩ አለመከናወን እና ተያያዥ ችግሮች ናቸው።

***<u>የተገኙ ትምህርቶች እና ወደፊቱ መደረግ ያለበት</u>***

- የምልመላ ስትራቴጂ እና መመሪያ ማዘጋጀት፣
- የሰው ሃይልና አቅም በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር፣
- ራሱን የቻለ ባለሞያ ያለው የዳታ ስራ ክፍል ማደራጀት እና የመረጃ አሰባሰብ በዚህ ስራ ክፍል እንዲመራ ማድረግ ይገኙበታል።

## *4.2.3 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ስልጠናን በተመለከተ*

***<u>ያጋጠሙ ችግሮች</u>***

- ሥልጠናው ለአንድ ቀን ብቻ መከናወኑ፣ ለአዲስ አስፈጻሚዎች በቂ ክህሎት ለመስጠት በቂ አለመሆኑ፣
- ለስልጠናው ዝግጅት የነበረው ጊዜ አጭር ከመሆኑ አንጻር የስልጠና ማኑዋል አስቀድሞ አለመድረሱ ሰልጣኞች በቂ ዝግጅት አድርገው እንዳይመጡ አድርጓል።

***<u>የተገኙ ትምህርቶች እና ለወደፊቱ መደረግ ያለበት</u>***

- የስልጠና ሂደት ስትራቴጂ እና የስልጠና ማኑዋል  በምርጫ ባለሙያዎች እና ሌሎች አካላት ጊዜ ሰጥቶ ቅድሚያ ማዘጋጀት

- ለወረዳ አስተባበሪ፣ ለምርጫ ጣቢያ ሀላፊ እና ለምርጫ አስፈጻሚ የተለየ ስልጠና ማዘጋጀት

## *4.2.4 የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ስምሪት*

**ያጋጠሙ ችግሮች**

- ስምሪቱ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ከፍተኛ የማስተባበር፣ የእቅድ እና በታሰበው መልኩ ያለመጓዝ ችግር የታየበት መሆኑ፣
- በተከታይም የስምሪቱ ችግር ከማእከል በተጨማሪ ሃዋሳ እና ወረዳዎችም ላይ የአስፈጻሚዎች ምደባ ችግር መፍጠሩ ናቸው፡፡

***የተገኘ ትምህርት እና ለወደፊቱ መደረግ ያለበት***

- ከማእከል አስፈጻሚዎችን የማሰማራት ስትራቴጂ ቀርፆ በአነስተኛ አቅም እና በተለያዩ ቦታዎች መከናወን አለበት፡፡

## *4.2.5 የምዝገባ እና ድምጽ መስጠት ሂደት ሰነድ ህትመት፣ ድልድል፣ ርክክብ እና ስርጭት*

**ያጋጠሙ ችግሮች**

- የምዝገባ ሂደት ሰነዶች መረካከቢያ ቅፅ፣ የመራጮች ካርድ፣ መዝገብ  እና መጠባበቢያ ቅፆች በበቂ መጠን በወረዳ ማስተባበሪያ አለመታሸግ፣ የእሽጋ እና ድልድል ስራው ብዙ ችግሮች ያሉበት መሆን ( የሰው ሃይል፣ የጊዜ፣ የቆጠራ ችግር...የመሳሰሉት) ፣
- የድምጽ መስጫ ወረቀት ህትመት፣ እሽጋ እና ስርጭት ደካማ እና ከምርጫ ሚስጥራዊነት መርሆ ጋር ያልታረቀ መሆን፣
- ለህትመት እና ድልድል አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች (የድምጽ መስጫ ሳጥን፣ ምርጫ ማረጋገጫ ቀለም፣ ዱፐሎ ቀለም፣ ማኒላ ወረቀት እና ቦንድ ወረቀት)በወቅቱ አለመሟላት ፣
- የዘገዩ ለውጦች መኖር የእሽጋ ስራውን በድጋሚ ማስጀመሩ፣
- የቦርዱ የህትመት ማሽኖች በሚገባ አለመስራት ናቸው፡፡

***የተገኙ ትምህርቶች እና ለወደፊቱ መደረግ ያለበት***

- የሰነዶች ድልድል እና እሽጋ ስራ በዝርዝር እቅድ የአሰራር ህግ መሰረት እንዲከናወን ማድረግ፣

- በአጠቃላይ የምርጫ ኦፐሬሽን ስራ የሰራተኞች አቅም ግንባታ እና የሰው ሃይልን ማስተካከል፣
- የሰነድ ህትመት፣ ድልድል እና እሽጋ በእቅድ ውስጥ በዝርዝር መከናወን ይኖርበታል።

## 4.2.6 በመራጮች ምዝገባ ሂደት ወቅት

**ያጋጠሙ ችግሮች**

- በምርጫ ጣቢያዎች በመራጮች ምዝገባ ቦታ መገኘት የሌለባቸው አካላት ታዛቢ፣ተቆጣጣሪ፣ አስተባባሪ በሚል መገኘታቸው፣
- ለመራጭነት ለመመዝገብ የሚያስፈልገው የመታወቂያ መስፈርት ላይ የግልጽነት ችግር መፈጠሩ፣
- ከምርጫ ጣቢያዎች የሚመጣው መረጃ ማስተላለፍ ሂደት ያልታሰበበት በመሆኑ መረጃዎችን የማጠናቀር ችግር፣
- የቅሬታ ሰሚ ኮሜቴ አመራረጥ በግልጽ ባለመቀመጡ በየምርጫ ጣቢያው የተገኙ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት አመራረጥ ግልፅ አለመሆን፣
- በምርጫ ጣቢያ የአንድ ወገን ወኪል ብቻ መገኘት እና የሌላኛው ወገን አለመኖር ናቸው።

***የተገኘ ትምህርት እና ለወደፊቱ መደረግ ያለበት***

- ከታዩ ችግሮች ትምህርት በመውሰድ የአስፈጻሚዎች ስልጠናን አስፈላጊ ርእሶች ( መታወቂያ፣ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ...) ላይ ትኩረት በማድረግ ማሻሻል፣
- የተጠና ከምርጫ አስፈጻሚዎች ተነስቶ በየደረጃው የሚሄድ የመረጃ መለዋወጫ መመሪያ መፍጠር ያስፈልጋል።

## 4.2.7 በድምፅ መስጫ ቀን

**ያጋጠሙ ችግሮች**

- በአንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች የተመዝጋቢ ቁጥር መብዛት እና ረጃጅም ሰልፎች መኖር፣
- በአብዛኛው ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የድምፅ መስጫ ወረቀት እጥረት እና የምርጫ ማረጋገጫ ቀለም መድረቅ፣
- የምርጫ አስፈፃሚዎች የማስፈጸም አቅም ችግሮች ( የካርድ፣ የመዝገብ አጠቃቀም)፣
- በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ከምርጫ ህጉ ውጪ ከ12፡00 ሰዓት  በፊት ቆጠራ መጀመር።

***<u>የተገኙ ትምህርቶች እና ለወደፊቱ መደረግ ያለበት</u>***

- የምርጫ አስፈጻሚዎችን አቅም ማጎልበት እና የሂደቱ መሪ ሆነው እንዲሰሩ ማስቻል፣
- የድምጽ መስጫ ቀንን አስመልክቶ የተለየ የመጠባበቂያ እቃ ስርጭት እቅድ ማውጣት።

## 4.2.8 በምርጫ አስፈፃሚዎች አስተዳደር

**<u>ያጋጠሙ ችግሮች</u>**

- የአስፈጻሚዎች የምርጫ ማስፈጸሚያ ስራ ቋንቋን አለመቻል፣ ስራ ቦታ መጥፋትና የተጨማሪ ክፍያ ጥያቄ፣
- የአስፈጻሚዎች ከፍተኛ የዲሲፕሊን ጥሰት፣ የምርጫ ካርድ ይዞ ቤት መሄድ፣ መዝገብ ይዞ ሲጓዙ መገኘት፣ ከገለልተኝነት መርህ ጋር በሚቃረን መልኩ ከወረዳ አስተዳደር ጋር በጋራ መስራት፣
- የምርጫ ሰነዶችን ህጋዊ ጥቅምና አሰራር አለመረዳት።

***<u>የተገኙ ትምህርቶች እና ለወደፊቱ መደረግ ያለበት</u>***

- የአስፈጻሚዎች ምልመላ እነዚህን ችግሮች ባገናዘበ መልኩ እንዲሆን ማድረግ፣
- የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ አካሄድ በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ማድረግ እና የምልመላ ስትራቴጂ ዶክመንት ማዘጋጀት።

## 4.2.9 የድምፅ ቆጠራ ውጤት አሞላል፣ አላላክ እና ይፋ አደራረግ

**<u>ያጋጠሙ ችግሮች</u>**

- የውጤት አስተዳደርን ከግምት ውስጥ ያስገባ ዝግጅት አለመደረጉ፣
- የተመዘገበው እና ድምፅ የሰጠ በአግባቡ ከመዝገብ ላይ አለመሞላቱ እና ድምጽ የመደመር ችግር መከሰቱ፣
- ውጤቱን የሚያዳምረው ሰው አለመታወቁ፣
- የሚፈለገው መረጃ በግልፅ አለመታወቁ፣
- አስቀድሞ ውጤቱን በቀላሉ ለመግለፅ የሚያስችል ሶፍትዌር አለማዘጋጀት፣
- ለምርጫ አስፈጻሚዎች በውጤት  አስተዳደርና አሞላል ዙሪያ በቂ ስልጠና አለመስጠት።

***<u>የተገኙ ትምህርቶች እና ለወደፊቱ መደረግ ያለበት</u>***

- የምርጫ ውጤት አላላክ እና አያያዝን በቴክኖሎጂ ማገዝ፣
- የምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠና ሲካሄድ የውጤት አስተዳደርን አስመልክቶ ልዩ ትኩረት መስጠት፣
- ለምርጫ አስፈፃሚዎች በውጤት አሞላል ዙሪያ በተግባር የተደገፈ ስልጠና ማድረግ እና የተጠያቂነት ስርአትን ማበጀት፣
- የዳታ እና ውጤት አስተዳደር ስርአትን መዘርጋት እና ባለሙያ ማሰልጠን ያስፈልጋል።

# ምዕራፍ ስድስት

## ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሲዳማ የክልልነት ህዝበ ውሳኔን የሚረዱ የተለያዩ ቅድመ ዝግጅቶችን አከናውኗል። በዚሁ መሰረት ለህዝበ ውሳኔው ማስፈጸሚያ ዝርዝር ዕቅድና በጀት ማዘጋጀትና ለድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ እንዲሁም ለድምጽ አሰጣጥ ቆጠራ እና ውጤት አገላለፅ የተለያዩ ቅፃቅፆች የማዘጋጀት ሥራ ሠርቷል። በተጨማሪም የህዝበ ውሳኔ ማስፈፀሚያ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት፣ሕዝበ ውሳኔው በተሳካ ሁኔታ እንዲከናወን የክልሉ መንግስት ባለስልጣን፣ የዞኑ አስተደዳር አካላት፣በተለያየ ደረጃ ከሚገኙ የፌደራል ፣የክልሉ፣የዞኑ እና የሀዋሳ ከተማ ፀጥታ አካላት ጋር ውይይቶች ማድረግና፣ የወረዳ እና የምርጫ ጣቢያ የምርጫ አስፈጻሚዎች ማሟላት እና ለምርጫ አስፈፃሚዎች ስልጠና መስጠት እና ሌሎችንም ስራዎችን በቅድመ ምርጫ ወቅት በአጥጋቢ ሁኔታ አከናውኗል።

ለድምፅ ሰጪዎች ለምዝገባ የሚያገለግሉ የተለያዩ ቅፆችና ሰነዶችን በማተም፣በቂና የተሟላ የሰው ኃይል በማደራጀት፣ ሰነዶችንና ቁሳቁሶችን በመደልደል እና በሲዳማ ዞን በሚገኙ 15 የወረዳ ማስተባበሪያዎች በማሰራጨት የመራጮች ምዝገባን በወጣው የምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አከናውኗል።

ለድምፅ አሰጣጥ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ ሂደት የሚያገለግሉ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች፣ ፖስተሮች፣ ሌሎች ሰነዶችን በማተም፣ የምርጫ ቁሳቁሶችን ጨምሮ የመደልደል፤ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ከአገር መከላከያ ሰራዊት ጋር በመተባበር ስርጭትን አከናውኗል።

በሲዳማ ህዝበ ውሳኔ በርካታ ተግባራት በአጥጋቢ ሁኔታ የተከናወኑ ሲሆን የህዝበ ውሳኔው ውጤት እና ሂደት ተአማኒነት ላይ ጉዳት ባያደርሱም በሥራው ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ነበሩ። ከነዚህም መካከል የምርጫ አስፈጻሚዎች አመላመል፣መረጣ እና ስምሪት፣ የውጤት አስተዳደር እና የመረጃ ፍሰት ችግሮች ዋናዎቹ ናቸው ። በሂደቱም የምርጫ ኦፕሬሽን ስራ ክፍል እና ሰራተኞች ከፍተኛ የአቅም ግንባታ እንደሚያስፈልግ ትምህርት ተወስዷል።

# ምስጋና

በ2012 ዓ.ም. የተካሄደው የሲዳማ የክልልነት ህዝበ ውሳኔ በተሳካ ሁኔታ ለማስፈፀም አድካሚ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ የምርጫ ሥራ ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል፣ ጉልበት፣ እውቀት እና ክህሎት ይጠይቃል፡፡ በዚሁ መሠረት በርካታ ባለድርሻ አካላትና ባለሙያዎች ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ በማድረጋቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

በዚሁ መሰረት

- በየወረዳው እና በየምርጫ ጣቢያው ተመድበው ህዝበ ውሳኔውን ላስፈፀሙ የምርጫ አስፈፃሚዎች
- የህዝበ ውሳኔውን ለታዘቡ ሲቪክ ማህበራት እና የውጪ ታዛቢዎች
- የህዝበ ውሳኔው ያለምንም የፀጥታ ችግር እንዲካሄድ እንዲሁም ሰነዶችን እና ምርጫ አስፈጻሚዎችን በማጀብ እና ጥበቃ በማደረግ ድጋፍ ላደረጉ የፌደራል ፖሊስ፣የመከላከያ ሚኒስቴር፣የክልሉ ፀጥታ ቢሮ እና የዞኑ ፖሊስ
- የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ
- ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና ለኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ
- ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ
- ለአዲስ አበባ ከተማ ሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት
- ለሲዳማ ዞን አስተዳደር
- ለሀዋሳ ከተማ አስተዳደር
- ለአይ ኤፍ ኤስ (IFES) ድርጅት እና ሰራተኞች
- እንግዶችን ተቀብሎ በሀገሩ ባህል እና ወግ መሰረት ላስተናገደ ለሲዳማ ዞን ህዝብ

ለምርጫ ቦርድ ሠራተኞች እና ለተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም የምርጫ ስራዎች የድጋፍ ፕሮጀክት (UNDP-SEEDS) የምርጫ ቦርድ አማካሪዎች ሙያዊ እውቀታቸውን፣ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን ያለምንም ማቅማማት ለዚህ ህዝበ ውሳኔ መሳካት አስተዋጽኦ በማድረጋቸው ቦርዱ ከፍተኛ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡